በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት የሥነ- ምግባርና
የፀረ ሙስና ኮሚሽን

# የሥነ-ምግባር አውታሮች የትብብርና የቅንጅት ፎረም ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

2014 ሀዋሣ

## በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባር አውታሮች የትብብርና የቅንጅት ፎረም ለማቋቋምናአሠራሩን ለመወሰን በድጋሚ ተሻሽሎ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር ……../2014

## መግቢያ፣

*ይህን መመሪያ ማሻሻልያስፈለገበት ምክንያት፡-*

- *የሥነምግባር አውታሮች ተልዕኳቸውን ለመወጣት በሚያደርጉት ጥረት በተቀናጀ፣ የትብብርና የግንኙነት አግባብ የሚታየውን ክፍተት በመሙላት በመካከላቸው የሚኖረውን የጉንዮሽና የተዋረድ ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር በማስፈለጉ፣*
- *ኮሚሽኑ በመንግሥት መ/ቤቶች በልማት ድርጅቶች፣ በህዝባዊ ተቋማት እንዲሁም በክልሉ ህብረተሰብ ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር በማስረፅ፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የሚታመንባቸው የሥነምግባር አውታሮች በፀረ-ሙስና ትግል ዙሪያ የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮቶች በጋራ ሆነው መፍትሔ መፈለግ የሚያስችላቸውን መድረክ መፍጠር በማስፈለጉ፣*
- *የሥነ-ምግባር አውታሮች በየተቋማቱ እና በህብረተሰቡ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል እና መልካም ሥነምግባርን የማስረፅ ተግባራቸውን ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ እንዲሁም ድግግሞሽ በማይፈጥር መልኩ እንዲያከናውኑ ለማስቻል፣*

በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 142/2004 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የሥነምግባር አውታሮች ስለሚደራጁበትና ሰለሚሠሩበት ሁኔታ ለመደንገግ በወጣው ደንብ ቁጥር 84/2003 ክፍል 3 አንቀፅ 4 መሠረት የክልሉ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም ያወጣውን የትብብርና ቅንጅት ፎረም መመሪያ በድጋሚ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

**<u>አንቀጽ፩.</u>**<u>አጭር ርዕስ፣</u>

ይህ መመሪያ «የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሥት የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የሥነ ምግባር አውታሮችየትብብርና የቅንጅት ፎረም ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን በድጋሚተሻሽሎየወጣመመሪያ ቁጥር ……/2014 »ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪</u>**<u>ትርጓሜ፣</u>

**የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣**

፩«**ኮሚሽን »ማለት** የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልየሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማለት ነው፡፡

፪«ተቋም» ማለት በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ሲቪል ማ/ሰብ፣ መገናኛ ብዙሃን እና የግሉ ዘርፍ ማለት ነው፡፡

፫«የመንግሥት መሥሪያ ቤት» ማለትበክልሉ መንግሥት በጀት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚተዳደርና የክልሉ መንግሥት ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

፬«**ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት**»ማለት በክልሉ የሚገኙ የመንግሥትዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆችማለት ነው፡፡

፭«የሥነ ምግባር አውታር» ማለት በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ በመንግሥት መ/ቤቶችና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ ምግባረ ብልሹ ባህርያትን ለመቀነስ፣መልካም ሥነ ምግባርን ለማስረጽና የፀረ ሙስና ትግሉን ለማስፋፋት የሚሠሩ አደረጃጀቶችን እና ሥርዓቶችን ያጠቃልላል፡፡

፮‹‹**ጥምረት**›› ማለት ሙስናን በተባበረ ኃይል በጋራ ለመታገል ከመንግሥት፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከግሉ ዘርፍና ከሲቪል ማህበረሰብ የተወጣጡ አካላት በፈቃደኝነት የመሠረቱት ክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት እና በቻርተሩ መሠረት በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የተመሠረቱና የሚመሰረቱ የፀረ-ሙስና ጥምረቶች ናቸው፡፡

፯‹‹**የሥነምግባርኦፊሰር**›› **ማለት** የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያ ሆኖ የሚያገለግል ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

፰‹‹**የፀረሙስናንቅናቄመድረክ ›› ማለት**ተቋማት እና በሕዝባዊ ማህበራት ተደራጅተው ለፀረ ሙስና ትግል ከኮሚሽኑ ጐን አጋር ሆነው የሚሰሩ ከሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀቶች የተቋቋመ አውታር ነው፡፡

፱‹‹**ፌዴሬሽን›› ማለት** በሴቶችና ወጣቶች የተቋቋሙ የተለያዩ አደረጃጀቶች በጋራ ስምምነት የፈጠሩት አንድነት ማለት ነው፡፡

፲ ‹‹**ፎረም ›› ማለት** በክልሉ በየደረጃው ባሉት የአስተዳደር እርከኖች የተደራጁ የሥነ-ምግባር አውታሮች የሚያካሄዱትን የፀረ-ሙስና ትግል በትብብርና በቅንጅት ይበልጥ አጠናክረው ለማካሄድ የሚያስችል የጋራ መድረክ ነው፡፡

፲፩ ‹‹**ፎካል ፐርሰን›› ማለት** የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በሌላቸው የፀረ-ሙስና ጥምረት አባል ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር ጉዳዮችን ከመደበኛ ሥራው ጋር ደርቦ እንዲያስተባብርና እንዲከታተል የተመደበ ባለሙያ ማለት ነው

## አንቀጽ ፫. ‹‹ፆታ አገላለጽ››

በዚህ መመሪያ ለወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## አንቀጽ ፬.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ በየደረጃው በተቋቋሙ የሥነ ምግባር አውታሮች የትብብርና የቅንጅት ፎረም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፭. መርህ

፩. የፎረሙ አመራር አካላት እና አባል አውታሮች መመሪያውን የማክበርና የማስከበር የመፈጸም እና የማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፣

፪. የፎረሙ አባል አውታሮች የህዝብና የመንግሥት አገልግሎት በሥነ ምግባር የታነፀ፣ ከሙስናና ብልሹ አሠራር የፀዳ እንዲሆን የግልጽነትና የተጠቂነት ሥርዓትን የማስፈን ኃላፊነት አለባቸው፣

፫. ሙስናና ብልሹ አሠራርን የሚፀየፉ እና በመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች የተገነቡ ተቋማትና ማህበረሰብ የመፍጠሩን ተግባር ሁሉም የሥነ ምግባር አውታሮች በጋራና በመተባበር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡፣

፬. የፎረሙ አባላት ተግባራቸውን  በተቀናጀ ሁኔታ ያከናውናሉ፡፡

## አንቀጽ ፮የመመሪያው ዓላማ

በክልሉ በተለያዩ እርከኖች የተደራጁ የተለያዩ የሥነ ምግባር አውታሮች በየበኩላቸው እያካሄዱ ያሉት የፀረ-ሙስና ትግል እንደተጠበቀ ሆኖ የጎንዮሽና የተዋረድ ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር በጋራ አፈፃፀማቸውን እየገመገሙ ጥንካሬዎችንና ጉድለቶችን በመለየት ጥንካሬዎችን በተሻለ ሁኔታ በማስቀጠልና በማስፋት፣ ድክመቶችን ደግሞ በጋራ በማረም ቀጣይ አቅጣጫ በማስቀመጥ የፀረ-ሙስና ትግሉን ሕዝባዊና ተቋማዊ መሠረት ማጠናከር ነው፡፡

## አንቀጽ ፯. የፎረሙ ዋና ዋና ተግባራት

**ፎረሙ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡**

፩በየአካባቢው የሚገኙ መንግሥታዊ ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣የሲቪል ማኅበረሰብ የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የግሉ ሴክተር የፀረ-ሙስናውን ትግል የየዕቅዳቸው አካል በማድረግና በማስተሳሰር እንዲተገብሩ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፣

፪.በየአስተዳደር እርከኑ በተናጠል እና በጋራ በሚካሄዳው የፀረ-ሙስና ትግል እየተመዘገበ ያለውን አፈፃፀም በመገምገም ትግሉን የሚያደናቅፉ ማነቆዎችን በጋራ መለየትና ማነቆዎቹ የሚፈቱበትን ስልት በመቀየስ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣

፫. በየአውታሮቹ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋፋት፣

፬. የሥነ ምግባር አውታሮች የሚያካሂዱት የፀረ-ሙስና ትግል በበጀትና ቁሳቁስ እንዲደገፍ ከተለያዩ አካላት ሀብት ማፈላለግ፡፡

፭. በአንድ አካባቢ የተደራጁ የሥነ ምግባር አውታሮች የጋራ ግንባር በመፍጠር የጐንዮሽና የተዋረድ የተቀናጀ የፀረ-ሙስና ትግል እንዲያካሄዱ ማድረግ፣

፮. ሙስናና የሥነ ምግባር ጉድለት በኅብረተሰቡ ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት በየአውታሮች የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በትክክል እንዲተገበርና ተከታታይ እንዲሆን ማድረግ፣

፯. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ተቋማት ሙስና በሀገርና በኅብረተሰብ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡና በዚህ ዙሪያ በአውታሮቹ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንዲደግፉ በተቀናጀ መልኩ ማነሳሳት፣

፰. የሁሉም የሥነ ምግባር አውታሮች አመራር አካላት የፀረ-ሙስና ትግሉን በቁርጠኝነትና በተነሳሽነት እየመሩ መሆኑን በትብብርና ቅንጅት መድረኩ መገምገምና ቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠርና ድጋፍ ማድረግ፡፡

፱. የፀረ-ሙስናውን ትግል ከሚደግፉ ሌሎች አካላት ጋር በትብብር መሥራት፣

፲፩. የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያጠናክሩ አዳዲስ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፣

፲፪. የፎረሙን የጋራ ዕቅድ መርምሮ ማጽደቅ፣

፲፫. የፎረሙ የጋራ መድረክ አመራር አካላት የሚያቀርቡትን ሪፖርት በ3 ወር እየተሰበሰበ ማዳመጥ፣ መገምገም፣ ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማሰተላለፍ፡፡

፲፬. የሥነምግባር አውታሮች በተቋማቱ እና በኅብረተሰቡ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል አና መልካም ሥነ ምግባርን የማስረፅ ተግባራቸውን ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ አንዲሁም ድግግሞሽ በማይፈጥር መልኩ እንዲያከናውኑ ማድረግ፣

፲፭. ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል በሚደረገው የፀረ-ሙስና ትገል በአውታሮች መካከል የሚኖረውን ትብብር ማጠናከር፣

፲፮. ለፎረሙ የተቀናጀ አሠራር የሚጠቅሙ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ማከናወን፣

# ክፍል ሁለት
## አደረጃጀት

### አንቀጽ ፰የፎረሙ አባላት አደረጃጀት

### ፩. በክልል ደረጃ፡-

ሀ. የክልሉ ፀረ ሙስና ጥምረት ሴክሬታሪያት፣

ለ. የክልሉ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ሐ. በክልል ደረጃ ባሉ ተቋማትና ልማት ድርጅቶች ውስጥ የተደራጁ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰሮች፣

1. ቴክኒክና ሙያ ትም/ሥ/ቢሮ
2. ትምህርት ቢሮ
3. ገቢዎች ቢሮ
4. ጤና ቢሮ
5. ግብርና ምርምር
6. ሠላምና ፀጥታ ቢሮ
7. ማረሚያ ቤቶች አስ/ኮሚሽን
8. ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን
9. ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
10. ፋይናንስ ቢሮ
11. ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ
12. ጠቅላይ ፍርድ ቤት
13. ግብርና ቢሮ
14. ፖሊስ ኮሚሽን
15. ክልል ምክር ቤት
16. መንገዶች ባለሥልጣን
17. ፍትሕ ቢሮ
18. ሴራዴፍ
19. ሬዲዮና ቴሌቪዥን
20. ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ
21. ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ
22. መስኖ ተቋማት ኤጀንሲ
23. ውሀ ማዕድንና ኤነርጂ ቢሮ
24. ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን
25. ዋናው ኦዲተር መ/ቤት
26. ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ
27. ኢንቨስትመንት ቢሮ
28. ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ
29. ሚሊሻ ጽ/ቤት

30.ፍትሕ አካላት ባለ/ሥ/የሕ/ምርምር ማዕከል
31.ደቡብ ውሃ ሥራዎች
32.ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ
33.ኘላን ኮሚሽን
34.ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
35.አርብቶ አደር ጉዳዮች ቢሮ
36.ሥራ ዕድል ፈጠራ
37.ባህልና ቱሪዝም ቢሮ
38.ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

መ. በክልሉ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክተሮች ያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

## ፪. በዞን ደረጃ፡-

ሀ. በዞኑየተደራጁ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎች

ለ. የዞኑ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ሐ. በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የሥነ ምግባር መኮንኖች፣ የመምህራን ትምህርት፣ የግብርና፣ የጤና ሳይንስ እና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ውስጥ የተደራጁ የሥነ ዜጋ እና ሥነምግባር ክበባት አመራሮች፣

መ. በዞን የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎች ያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

## ፫. በልዩ ወረዳ ደረጃ

ሀ. በልዩ ወረዳየተደራጁ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎች

ለ. የልዩ ወረዳ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ሐ. በልዩ ወረዳ በሚገኙ ኮሌጆች/ተቋማት፣ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤቶች የተደራጁ የሥነዜጋእናየሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፣

መ. በልዩ ወረደው የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎችያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

ሠ. በልዩ ወረዳ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በዋና ከተማ ውስጥ የሚገኙ 2ኛ ሣይክል የተደራጁ የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፡፡

## ፬. በወረዳ ደረጃ

ሀ. በወረዳውየተደራጁ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎች፣

ለ. የወረዳ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ሐ. በወረዳ በሚገኙ ኮሌጆች/ተቋማት፣ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤቶች የተደራጁ የሥነ ዜጋ እና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፣

መ. በወረደውየሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎችያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

ሠ. በወረዳው ዋና ከተማ ውስጥ የሚገኙ 1ኛ ደረጃ 2ኛ ሣይክል የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች

## ፭. በ21 ሪፎርም ከተማ አስተዳዳር ደረጃ

ሀ. በከተማ አስተዳደር የተደራጁ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎች፣

ለ. የከተማ አስተዳደሩ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ሐ. በከተማ አስተዳደር በሚገኙ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤቶች የተደራጁ የሥነ ዜጋ እና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፣

መ. በከተማ አስተዳደርየሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪዎችያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

ሠ. በከተማ አስተዳደር በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በ2ኛ ሣይክል የተደራጁ የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፡፡

## ፮. በቀበሌ ደረጃ

ሀ. የቀበሌ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች፣

ለ. በቀበሌው የሚገኙ ት/ቤቶች ውስጥ የተደራጁ የሥነ ዜጋና የሥነ ምግበር ክበባት አመራሮች፣ ት/ቤቶች በማይገኙባቸው ቀበሌያት የወጣቶች ፌዴሬሽን አመራሮች፣

ሐ. በቀበሌ ደረጃ የሚደራጁ የፀረ-ሙስና ጥምረት አመራሮች፣

መ. የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች፡፡

# ክፍልሦስት
## በየደረጃዉ የአውታሮች ፎረም የትብብርና የቅንጅት ስለመመስረት

### አንቀጽ ፱. የፎረሙ መመስረት

፩. በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 142/2004 እንዲሁም በክልሉ የሥነ ምግባር አውታሮች ስለሚደራጁበትና ስለሚሠሩበት ሁኔታ ለመደንገግ የወጣውን ደንብ ቁጥር 84/2003 እና ይህን መመያ መሠረት አድርጐ በክልል፣ በዞኖች፣ በልዩ ወረዳዎች፣ በወረዳ፣ በሪፎርም ከተማ አስተዳደሮች እና በቀበሌ ደረጃ የሥነ ምግባር አውታሮች የትብብርና የቅንጅት የጋራ ፎረሞች ይቋቋማሉ፡፡

፪. በየደረጃው ያሉ የሥነ ምግባር አውታሮች የትብብርና የቅንጅት ፎረሙን ለማቋቋም በሚያደርጉት ጥረት ኮሚሽኑ አስፈላጊውን የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፣

፫. የፎረሙ መመሥረት ይፋ የሚደረገው በየደረጃው በተደራጁ የፎረሙ አመራር አካላት ይሆናል፣

፬. የፎረሙ ምሥረታ ይፋ የሚደረገው የፎረሙ አባል አዉታሮች አመራርና ተወካይ ባለሙያዎች /Focal person/ ስብሰባ መጥራት ይሆናል፣

### አንቀጽ ፲.የፎረሙ የጋራ መድረክ እና አቋም

ፎረሙ የጋራ መድረክ እና የመድረክ አመራር አካላት የሚኖረዉ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አደረጃጀቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

### ፲.፩የፎረሙ የጋራ መድረክ

ፎረሙ ከክልል እስከ ወረዳ/ከተማ እና ቀበሌ አስተዳደር ድረስ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች የተደራጁ /የሚደራጁ/ የሴቶችና ወጣቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረክ አመራሮች የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አመራሮች፣ የሥነ ምግባር መከታተያ ኦፊሰሮች እና የፀረ-ሙስና ጥምረቱን ሥራ ደርበው እንዲሠሩ የተመደቡ ባለሙያዎች የሚሳተፉበት የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡

### ፲.፪ የትብብርና ቅንጅት ፎረሙ አቋም

የሥነ-ምግባር አውታሮች የትብብርና ቅንጅት ፎረም የሚከተለው አቋም ይኖረዋል፡-

ሀ. ሰብሳቢ
ለ. ም/ሰብሳቢ
ሐ. ፀሐፊ
መ. አባላት

## ***አንቀጽ ፲፩.የሥነ ምግባር አውታሮች የትብብርና ቅንጅት ፎረም አመራር አካላት***

***፲፩.፩በክልልደረጃ፡-***

ሀ. የኮሚሽኑ የሥነ ምግባር አውታሮች ማስ/ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፡- ሰብሳቢ

ለ. የክልሉሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ፡- ም/ሰብሳቢ

ሐ. በየዓመቱ የላቀ አፈጻጸም ያስመዘገበ ተቋም የሥ/ፀ/ሙስና ዳይሬክተር፡- ፀሃፊ

መ. በክልሉ በሁሉም ተቋማት የተመደቡ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክተሮች የፎረሙ አባል ይሆናሉ፡፡

***፲፩.፪ በዞን ደረጃ፡-***

ሀ. የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የስነምግባር ኦፊሰር፡- ሰብሳቢ

ለ. የዞኑ ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች መምሪያ ኃላፊ፡- ም/ሰብሳቢ

ሐ. የዞን ፋ/ኢ/ል/ መምሪያ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ፀሓፊ

መ. የዞኑ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ኦፊሰር፡- አባል

ሠ. በዞን የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ ያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

***፲፩.፫ በልዩ ወረዳ ደረጃ፡-***

ሀ. የልዩ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ሰብሳቢ

ለ. የልዩ ወረዳው ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ፡- ም/ሰብሳቢ

ሐ. የልዩ ወረዳዉ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ፀሓፊ፣

መ. በልዩ ወረዳ የሚገኙ ከ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አንድተወከይ፡- አባል

ሠ. የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

***፲፩.፬ በወረዳ ደረጃ፡-***

ሀ. የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ሰብሳቢ

ለ. የወረዳው ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ፡- ም/ሰብሳቢ

ሐ. የወረዳዉ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ፀሓፊ፣

መ. በወረዳ የሚገኙ ከ/2ኛ ደረጃ መሰናዶ ት/ቤቶች የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አንድ ተወከይ፡- አባል

ሠ. በወረዳው የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ ያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ

ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

***፲፩.፫ በሪፎርም ከተሞች፡-***

ሀ. የከንቲባ ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ሰብሳቢ

ለ. የከተማው ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ፡- ም/ሰብሳቢ

ሐ. የከተማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር፡- ፀሐፊ

መ. በከተማ ከሚገኙ ከ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት አንድ ተወከይ፡- አባል

ሠ. የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪያልተመደቡባቸው ተቋማት በመደቡ ወቅት የፎረሙ አባላት ይሆናሉ፡፡

***፲፩.፬ በቀበሌ ደረጃ***

ሀ. የቀበሌ ስራ አስኪያጅ፡- ሰብሳቢ

ለ. የቀበሌ ሴቶችና ወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረክ ሰብሳቢ፡- ም/ሰብሳቢ፣

ሐ. በቀበሌው በሚገኙ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከተደራጁ የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ክበባት ሁለት ተወካዮች አንዱ ፀሐፊ፣ ት/ቤቶች በሌሉባቸው ቀበሌያት የወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ፡- የፎረሙ ፀሐፊ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# የፎረሙ አመራር አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## አንቀጽ ፲፪. የትብብርና የቅንጅት ፎረም አመራር ተግባርና ኃላፊነት፡-

፩. በአውታሮች መካከል የልምድ ልውውጥ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፪. አውታሮቹ ለሚያደርጉት የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ በሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲሰጥ ያስተባብራል፣

፫. የፎረሙ አባል አውታሮች ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

፬. የፎረሙንዕቅድያዘጋጃል

፭. ለፎረሙ ዕቅድ መሳካት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣

፮. በየተቋማቱ መልካም ሥነ ምግባርን ለማስፈን በፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች ርዕሶች ላይ ለኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በትክክል መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፯. በፀረ-ሙስና ትግል የላቀ ውጤት ላስገኙ ተቋማት ወይም ግለሰቦች እውቅና እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፰. የሥነ ምግባር አውታሮች የጋራ ውይይትና ምክክር የሚያካሄዱበትና ልምድ የሚለዋወጡበትን መድረኮች ማመቻቸት፣

፱. ምርጥ ተሞክሮዎች በአባል አውታሮች እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

፲. የሥነምግባር አውታሮች የጋራ ውይይትና ምክክር የሚያካሄዱበትና ልምድ የምለዋወጡበትን መድረኮች ያመቻቻል፣

፲፩. በየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመገምገም ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፲፫.የፎረሙ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የፎረሙን ዕቅድ ከፀሐፊው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣

፪. የፎረሙን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ስብሰባ ይመራል፣

፫. ከፀሐፊው ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

፬. የመድረኩን ስብሰባ ይጠራል፣ ያወያያል፣

፭. በፎረሙ አመራር የተወሰኑ ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፮. የፎረሙን ዕቅድ እና ሪፖርት በአመራሩ ከፀደቀ በኋላ ለጋራ መድረኩ ያቀርባል

**አንቀጽ ፲፬.የፎረሙ ም/ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

፩. ሰብሣቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

፪. ሌሎች ከሰብሣቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

**አንቀጽ ፲፭.የፎረሙ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት**

፩የፎረሙን ዕቅድ ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፡፡

፪ የፎረሙ ሠነዶች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ያመቻቻል፣

፫ለፎረሙ አባላት የስብሰባ ጥሪ ደብዳቤ በማዘጋጀት ያሰራጫል፣

፬ለፎረሙ ስብሰባ የሚሆኑ አጀንዳዎችን ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣

፭በስብሰባ ሰዓት ቃለ፡-ጉባኤ ይይዛል፣

፮የፎረሙን ማንኛውንም ሠነዶች በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣ የሥራ ጊዜው ስያልቅ አድስ ለተመደበው ፀሐፊ ያስረክባል፣

፯በሪፖርት ዝግጅት ወቅት ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ይሰራል፣ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ጥረት ያደርጋል፣

፰ሌሎች በሰብሣቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፲፮የፎረሙ የግንኙነት አግባብ፡-

፩፥ ከክልል እስከ ወረዳ ከተማ እና ቀበሌ አስተዳደር የተቋቋመው ፎረም ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት በየሩብ ዓመት ከተዋረድ እየተቀበለ ቀጥሎ ላለው አካል ያቀርባል፣ ግብረ መልስ ተቀብሎ በተዋረድ ይሰጣል፣

፪፥ የፎረሙ አመራር ከክልል ጀምሮ በተዋረድ በዓመት ሁለት ጊዜ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣

፫፥ የፎረሙ አመራር አካላት በወር አንድ ጊዜ በቋሚነት እየተሰበሰቡ ስለሥራው ውይይት በማድረግ ከጠንካራ ጐኖች ልምድ ይለዋወጣሉ፣ ደካማጐኖች ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ የጋራ መፍትሄ ያስቀምጣሉ፣

፬፥ በየደረጃው ካለው መስተዳድር አስተዳደር አካላት፣ ከሌሎች ልዩ ልዩ ማህበራት፣ አደረጃጀቶች እና ተቋማት ጋር የፎረሙን ዓላማ ለማሳካት የሥራግንኙነት ያደርጋል፣ ድጋፍ ይጠይቃል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድጋፍ ይሰጣል፣

### አንቀጽ ፲፯.ከኮሚሽኑ የሚጠበቁ ተግባራት

፩፥ የፎረሙን አባል አውታሮች የመፈፀም አቅም የሚያጐለብቱ ተግባራትን ይፈፅማል፣

፪፥ የፎረሙ ዓላማ እንዲሳካ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ ፲፰. ስለመተባበር

በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 142/2004 እና የሥነ ምግባር አውታሮች ስለሚደራጁበትና ስለሚሠሩበት ሁኔታ በሚደነግገው የመስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 84/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ፎረሞቹ በሚቋቋሙበት አካባቢ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች፣ ሕዝባዊ ተቋማት እና ሌሎች አካላት ፎረሞቹ ለሚያከናውኑት ተግባር ሁኔታው የሚጠይቀውንና አቅማቸው የሚፈቅደውን የመተባበር ግዴታ አለባቸው፣

### አንቀጽ ፲፱. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና አሠራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች አሠራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀጽ ፳ተጠያቂነት

ይህን መመሪያ በማያከብሩ እና የተጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት ባልቻሉ የፎረሙ አመራር አባላት በወከሉት አደረጃጀት ውስጠ ደንብ መሠረት ይጠየቃሉ፣ ይህም ቀጥሎ ላለው የትብብርና የቅንጅት ፎረም እና ለኮሚሽኑ በግልባጭ ይገለጻል፡፡

## አንቀጽ ፳፩. መመሪያውን ስለማሻሻል

የክልሉ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፳፪መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለው መመሪያ ከየካቲት ……../2014 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አበራ ኪጴ**
የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት
የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን
ኮሚሽነር